

## የእኛ አሻራ

ከ1984 ጀምሮ የ Saint Paul & Ramsey County የቤት ውስጥ ጥቃት ፕሮጀክት (SPIP) የሚከተሉትን አድርጓል፦

- ለቤት ውስጥ ጥቃት ተጎጂዎች በባህል እና በቋንቋ ምላሽ ሰጪ የሆነ ተሟጋችነት፣ የቀውስ ጊዜ ጣልቃ ገብነት፣ ሕጋዊ አገልግሎቶች፣ እና ድጋፍ አቅርቧል
- ሥርዓቱ ለቤት ውስጥ ጥቃት የሚሰጠውን ምላሽ አስተባብሯል
- ለቤት ውስጥ ጥቃት ተጎጂዎች እና ለሰፊው ማኅበረሰብ ትምህርት፣ መከላከያ እና ስምሪት አቅርቧል
- የቤት ውስጥ ጥቃት እንዲያበቃ ማኅበረሰብ አቀፍ ምላሽ አዳብሯል

## እኛ ማን እንደሆንን

SPIP የቤት ውስጥ ጥቃት ተጎጂዎችን ለመርዳት በ1984 የተመሠረተ ማኅበረሰብ ተኮር ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው።

ሁሉም የጥቃት ተጎጂዎች በቤታቸው እና በመኖሪያ ሰፈራቸው ደኅንነታቸው ተጠብቆ የመኖር እንዲሁም ወደፊት ለመጓዝ እና ከጥቃት ነጻ ሆኖ ለመኖር ለእነሱም ለልጆቻቸውም አስፈላጊውን እርዳታ፣ አገልግሎቶች፣ እና መርጃዎች የማግኘት መብት አላቸው።

### እርዳታ ካስፈለገዎት እባክዎን ያነጋግሩን

የቢሮ የስልክ መሥመር እና የ24 ሰዓት ቀውስን የተመለከተ የስልክ መሥመር፦

**651-645-2824**

**888-575-3367**
(ነጻ የስልክ መሥመር)

***በትህትና*** *እና* ***በአክብሮት ይስተናገዳሉ።***
*ሁሉም አገልግሎቶች* ***ምስጢራዊ***
*እና* ***ከክፍያ ነጻ ናቸው።***

የ Saint Paul & Ramsey County የቤት ውስጥ ጥቃት ጣልቃ ገብነት ፕሮጀክት
394 Dayton Avenue | Saint Paul, MN 55102

AMHARIC

# ከጥቃት ነጻ የሆነ ወደፊት መገንባት።



St. Paul & Ramsey County
**Domestic Abuse Intervention Project**
"SPIP"

## የእኛ ተጽእኖ

በየዓመቱ በእኛ አፋጣኝ ጣልቃ ገብነት እና የሽግግር አገልግሎቶች፦

ከ 6,200በላይ የሆኑ የጥቃት ተጎጂዎች እና ልጆቻቸው በቀጥታ አገልግሎቶችን ያገኛሉ

ከ 4,700 በላይ የሆኑ የጥቃት ተጎጂዎች የየቤት ውስጥ ጥቃትን ተከትሎ ቀውስ ጊዜ ሕጋዊ ተሟጋችነት እና ወሳኝ ድጋፍ አገልግሎቶችን ወዲያውኑ ያገኛሉ

ከ 3,200በላይ የጥቃት ተጎጂዎች የሲቪል እና የቤተሰብ ፍርድ ቤት ተሟጋችነት አገልግሎቶችን እና መረጃ ያገኛሉ

ከ 600 በላይ የጥቃት ተጎጂዎች የጥበቃ ትእዛዝ (OFPs) ለማግኘት ድጋፍ አግኝተዋል

ከ8,000በላይ ድጋፍ፣ መረጃ እና ጥቆማ የሚጠይቁ ጥሪዎች በ24 ሰዓት የቀውስ ጊዜ የስልክ መሥመሮች ላይ ተደርገዋል

ከ 5,800 በላይ ተጎጂዎች እና ልጆቻቸው መሠታዊ እና የረጅም ጊዜ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ወሳኝ የሽግግር አገልግሎቶችን ያገኛሉ

ከማኅበረሰብ ተኮር እና ከመንግሥት ኤጀንሲዎች ጋር ያለን ጠንካራ አጋርነት በተጎጂዎች እና በልጆቻቸው ደኅንነት፣ የጥቃት አድራሾች ተጠያቂነት እና የመለወጥ እድሎች ላይ እንዲሁም ማኅበረሰባችን ለቤት ውስጥ ጥቃት ምላሽ በሚሰጥበት መንገድ ላይ ትልቅ ተፅእኖ አለው።

## የእኛ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

- የ24-ሰዓት የቀውስ ጊዜ የስልክ መሥመር
- 24-ሰዓት የአፋጣኝ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች
- ወደ ደኅንነት መሸጋገርያ *(ትብብራዊ)*
- የሲቪል የሕግ ጠበቃ አገልግሎቶች
- የማኅበረሰብ ስምሪት እና ትምህርት
- የቤተሰብ የሽግግር አገልግሎቶች
- አጠቃላይ እና ሕጋዊ የተሟጋችነት አገልግሎቶች
- የሆስፒታል/የክሊኒክ ተሟጋችነት አገልግሎቶች
- የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት
- St. Paul/ብሔራዊ *የደኅንነት ፍኖተ ካርታ*
- የሥርዓት ለውጥ ተሟጋችነት
- በባህል እና ቋንቋ ምላሽ ሰጪ የሆኑ አገልግሎቶች
- በእድሜ ለገፉ የጥቃት ተጎጂዎች የተለዩ አገልግሎቶች

## የእኛ ሠራተኞች

ልናገለግላቸው የምናስባቸውን ሰዎች ባህል፣ አኗኗር እና እውነታ በቅርበት በሚረዱ ሠራተኞች የተለያዩ፣ ባለ ብዙ ቋንቋ እና ባህላዊ ምላሽ ሰጪ የሆኑ ፕሮግራሞችን ማቅረባችንን ለማረጋገጥ እንጥራለን።

### SPIP ተጎጂ/ከጥቃት የተረፉ ሰዎች አገልግሎቶች

- የሽግግር አገልግሎቶች
- የ24 ሰዓት የቀውስ ጊዜ ጣልቃ ገብነት
- የሕፃናት ፍላጎቶች
- ሕግ ማስከበር
- ቀጣይነት ያለው ድጋፍ
- ደኅንነት
- የወንጀል ፍትህ ሥርዓት
- ፍልሰት
- የሕክምና የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች
- የገንዘብ ድጋፍ የሥራ ቅጥር
- ደኅንነቱ የተጠበቀ መኖሪያ ቤት ማግኘት/ይዞ መቆየት
- የሲቪል/የቤተሰብ ሕግ ጉዳዮች
- የጥበቃ ትእዛዞች

*"ልጆቼን እና ራሴን ለመጠበቅ ስላገዛችሁኝ (ሁላችሁንም) አመሰግናለሁ። ነገር ሁሉ በጨለመብኝ ጊዜ ለእኔ ልክ እንደ ፀሐይ ብርሃን... መተንፈስ ባልቻልኩበት ጊዜ ልክ እንደ እስትንፋሴ ነበራችሁ።"*

– ተጎጂ/ከጥቃት የተረፈ

